# የጥቅምት ግርግር ና የ ቄሮ ሽብር !!!!

የዚህ ሳምንት ግርግር መሪ ተዋንያኑ ጃዋር መሀመድ የድረሱልኝ ተከብብኤለሁ የማህበራዊ ገፅ ኡኡታ ተከታዮቹን የሚኖርበት ድረስ ሲያሰባስብ  የብዙ ህይወት መጥፋት ንብረት ቃጠሎ መንገድ መዝጋት በ ኦሮሞ ከተማዎች ተፈፅምዋል።

በዛሬው ዕለት ከ ኦሮሞ ተወካይ ነን ከሚሉ ጋር ሆኖ ተረጋጉ የሚል መመሪያ መሰል ጃዋር መሀመድ ካለበት ቤት ለጋዜጠኞች መሰጠቱን አይተናል።  ሽብሩን የማቀዝቀዝ ስራ ልክ ሽብሩን ካስነሳ በኋላ ማለት ነው።

 የቁም ዕስረኛ በማድረግ  ከተከታዮቹ  ለመነጠል መገናኛዎችን በመከልከል የሚጠፋውን ህይወትና ንብረት ማዳን ይቻላል።

የ ኦሮሞ ኢህዴግ ከ አዲስ አበባ ከራቁ ቦታዎች ህዝብ በማነቃነቅ በ ኢሬቻ 150 ያሳየው ህዝብ የማስፈራራት ዕንቅስቃሴ ሰሞኑን ጃዋር ካደረገው ድረሱልኝ ጋር  የ መንጋ ማስፈራራት ተመሳሳይ አሰራር ናቸው። በህዝብ ማዕበል ማሸበር ወይምየ ቄሮ ሽብር ሊባል ይችላል።

ይህን ዐይነት የመንጋ ጥሪ ናዝሬት ደብረ ዘይት ሀረር  ድሬዳዋ በ ተደጋጋሚ ታይትዋል። ህዝቡ ጥቃት ሲደርስበት የ ኦሮሞ ፖሊስ ደብዳቢና  ተደብዳቢ ሳይለይ በጥይት ብዙ ህይወት ጠፍትዋል በ ዘር ተኮል ጥቃት ከተገደሉት በተጨማሪ።

አዲስ አበባ ሰሞኑን ከሩቅ በመጡ መንጋዎች ስብሰባ ተበትንዋል ድብደባም ህይወት ማጥፋትም ተፈፅምዋል።

በመሆኑም አዲስ አበባና የ ኦሮሞ ክልል ያሉ ከተሞች በሙሉ ያሉ የ ኦሮሞ ፖሊስ ና ልዩ ሀይል ከህዝብ መራቅ ይኖርባቸዋል።

አዲስ አበባና ዙርያ መግቢያ መዉጫ በሙሉ በመከላከያ ቁጥጥር ስር መዉደቅ ግድ ይላል። በተመሳሳይ ናዝሬት ድሬዳዋ  ደብረ ዘይት ሀረር   ባሌ ጎባ በወታደራዊ ዕዝ መዉደቅ ይኖርበታል።

የ ኦሮሞ ልዩ ሀይልና ፖሊስ መንገዶች ደህንነት የማስጠበቅ ስራው በመከላከያ ስር ሆኖ መስራት አልያም መለዮውን አዉልቆ ከስራ ማሰናበት ይገባል።

የ አዲስ አበባ ነዋሪዎች ና ሌሎች ከተማዎች በ ኦሮሞ ክልል የሚገኙ ከ መከላከያሰራዊት ጋር በጋራ በመስራት የነዋሪውና ነብ'ዢዎችን ደህንነት በጋራ ለመጠበቅ  ጃዋር መሀመድ በህግ እስኪዳኝ ከጥቅም ዉጭ ለማድረግ መነቃነቂያ ጊዜ አሁን ነው።

ጃዋር መሀመድና ቄሮ አሸባሪዎቹ ለፈፀሙት ወንጀል ለፍርድ ካልቀረቡ ሀገራችንና ህዝብዋን ለ መታደግ የመከላከያ ሠራዊት ወደ ስልጣን እንዲመጣ ህዝቡ መጠየቁ አይቀሬ ይሆናል።

የጃዋር  መሀመድና የቄሮ ሽብር ህዝቡ በቃን ሲል ድምፁን ማሰማት ጀምርዋል መቀጠል ይኖርበታል።

**Tedla Asfaw**